# <u>ኑዛዜ አቀርባለሁ (ተስፋሁን ሞላ)</u>

ከላይ የታዘዘ ብሐር መዝገብ ይዞ
ወደ እኔ ይመጣል ሊጠይቅ አናዞ
አንድ በአንድ ይጽፋል ስራየን ቆጥሮ
የማያውቅ ይመስል እንዳልነበር አብሮ።
ከአለሁበት ድረስ ይመጣል አድኖ
እኔን ይዞ ሊሄድ በአንሶላ ሸፍኖ።
ጣረሞት ይዞኛል እንዳልንቀሳቀስ
መች ይቀራልና የሰው ሥጋ መፍረስ
በሁሉ ያለነው ሰው ሞቶ አፈር መቅመስ
የተጻፈነው ካፈር የተሰራ ወደ አፈር መመለስ።
ታሪክ ስርቻለሁ ሁሉጊዜ የሚያስታውስ
አይቆጨኝም እኔን ገብቶ አፈር ብለብስ።
ሃውልቴን ስሩልኝ ከሚያገኘው ጸሐይ
ዓይን የከፈተለት እየሄደን እንዲያይ
አደራ በምድር አደራ በሰማይ።
ሃውልቴን አቁሙት ከአራቱ ማእዘናት
የሚሄድ የሚመጣው ሁሉ እንዲመለከት
ይህ ኑዛዜ ነው አደራ እንዳትረሱት።
የሞትኩ እንኳን ብሆን የተጫነኝ አፈር
የሠራሁት ሥራ ይኖራል ሲናገር
ሃውልቴን አቁሙት እሱ እንዲመሰክር
አደራ እንዳይጠፋ ከቦታው የሰው ዘር
እውነት መናገር ነው መንጋቱ ላይቀር
የተሰራ ሥራ አይችል መጥፋት መሰወር።
አደራ ጻፉልኝ የሕይወት ታሪኬን
ህዝቡም እንዲያውቅልኝ አገር መገንባቴን።